# የኦሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ኅብረት (ኦሕዲኅ)
# Omo Peoples Democratic Union (OPDU)

ቁጥር፡ ኦሕዲኅ/ ደኦ/ 001/08 ቀን፡ ጥቅምት 19/2008 ዓ.ም

ለደቡብ ኦሞ ዞን አስተዳደር
ጂንካ፣

ጉዳዩ፡- **በዞናችን የሚታዩትን አሳሳቢ የሰብዐዊና ዲሞክራሲዊ መብት ጉዳዮች ይመለከታል፤**

ድርጅታችን የዞናችን ነዋሪዎችን ፖለቲካዊና ማህበረ-ኢኮኖሚ ህይወት ወደተሻለ ደረጃ ለማሳደግ ላለፉት 24 ዓመታት በሰላማዊ ትግል መርህ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ በነዚህ የትግል ዓመታት በዞናችን የሚደረጉትን እንቅስቃሴዎች በመከታተል ለገንቢ ተግባራት ድጋፋችንን እየገለጽን፣ በሚታዩ ችግሮችና ክፍተቶች ተቃውሞአችንና የመፍትሄ ኃሳባችንን እያቀረብን የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ሰላማዊ ትግል እያደረግን መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ የዞኑ መስተዳድርም ሆነ የክልሉና የፌዴራል መንግስት እኛን እንደጉዳዩ ባለቤትና ባለድርሻ እንዲሁም የምናቀርባቸውን ጥያቄዎች በአዎንታዊነት ተቀብለው የመፍትሄ ኃሳቦችን ባለመቀበላቸውና ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ኅብረተሰባችን በተለያዩ ጊዜያት የበርካታ ችግሮች ሰለባ ሲሆን በተደጋጋሚ በተጨባጭ የተመለከትነው ነው፡፡

ሆኖም በአዲሱ መንግስት ምስረታ ወቅት ፕሬዝዳንቱ ባሰሙት ንግግር እንዲሁም ጠቅላይ ሚ/ሩ “ከተቃዋሚዎች ጋር የምርጫ ወቅት ሳንጠብቅ በአገራዊ ጉዳዮች ለመወያየት …….” መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል፡፡

ስለዚህ ዛሬም በዞናችን የተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እየተስተዋሉ በመሆኑ አስፈላጊው የእርምትና የመከላከል እርምጃ ይወሰድ ዘንድ ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው ስናቀርብ በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት ችግሩን ተመልክተው ለመፍትሄው እንደሚተጉ ተስፋ በማድረግ ነው፡፡

## 1ኛ/ በዞናችን በተደጋጋሚ የሚታዩ ችግሮች፤

### 1.1. በሀመር ወረዳ በህዝብና መስተዳድሩ መካከል የተፈጠረው ችግር፡-

ይህን ችግር በሚመለከት የችግሩን አሳሳቢነትና ሊያስከትል የሚችለውን ማህበረ-ኢኮኖሚ ቀውስ በሚመለከት ስጋታችንን በተደጋጋሚ ገልጸናል፡፡ መፍትሄውም ችግሩን በአካባቢው በተለመደው የአገር ሽማግሌዎችን ባሳተፈ ውይይትና ዕርቅ የግጭት አፈታት ልምድ መሰረት መፍታት እንደሆነ ገልጸናል፡፡ ይሁን እንጂ መንግስት ችግሩን በኃይል ለመፍታት በወሰደው እርምጃ ችግሩ እስከዛሬ ሳይፈታ ከመዝለቁም በላይ ብዙ ህይወት እንዲጠፉ፣ ንብረት እንዲወድምና ማኅበራዊ አገልግሎት እንዲቋረጥ ሆኗል፡፡ ችግሩ በአሁኑ ወቅት ወደከፋ ደረጃ እያመራ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፤ በቅርቡም በ01/02/2008 በሰንበሌ ቀበሌ የወረዳው ማዘጋጃ ቤት ገቢ ሰብሳቢ አቶ ወንድማገኝ ላይ የተፈጸመውን ግድያና በወረዳው አስተዳዳሪ አቶ አወቀ አይኬ ላይ የመግደል ሙከራ መደረጉንና የመንግስት ሠራተኞች ባነሱት የደህንነት ዋስትና ጥያቄ በተገናኘ ማኅበራዊ አገልግሎቶች እንደተቋረጡ መሆኑን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ እንዲህ ባለበት መንግስት በአካባቢው ካሰፈረው የፌዴራልና ክልል ኃይል ችግሩን መፍታት ባለመቻሉ፣ የመንግስት ካድሬ የሆኑ የሀመር ወጣቶችን በአካባቢ ሚሊሺያ ስም አሰልጥኖ የመብት ጥያቄ ካቀረቡ ወንድሞቻቸው ጋር ለማጋጨት እየተዘጋጀ መሆኑ እየተነገረ ነው፡፡ይህም የወንድም ለወንድም ግጭት በመፍጠር ማኅበራዊ ቀውሱን ከማባባስ አልፎ ለችግሩ መፍትሄ አይሆንም፡፡ በዚህ ሁኔታ አካባቢው በድርቅ እየተጎዳ ባለበት የዕለት ደራሽ ሰብዐዊ

ዕርዳታ ሊያገኝ አይችልም፡፡ ስለዚህ ዛሬም ለዚህ ችግር በህዝቡ በተለመደው አሳታፊ የግጭት አፈታት መንገድ ዘላቂ መፍትሄ እንዲበጅለት፤

## 1.2. በዞናችን በመቋቋም ላይ ካለው የስኳር ፕሮጀክት ጋር የተያያዙ ችግሮች፡-

በዞናችን በሳላማጎ ወረዳ በመገንባት ላይ ካለው የስኳር ልማት ፕሮጀክት ጋር በተገናኘ በተደጋጋሚ የውጪ ዜጎችን ጨምሮ የሰው ህይወት ሲቀጠፍ ተመልክተናል፤ይህን ዓይነቱ ችግር ከፕሮጀክቱም አስቀድሞ ሰፈራ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የተከሰተ ቢሆንም ከዚህ ፕሮጀክት ትግበራ መጀመር ጋር እየተባባሰ መምጣቱ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ መነሻውም ሰፈራውም ሆነ ፕሮጀክቱ ከዕቅድ ጀምሮ ከወረዳው ነዋሪዎች ጋር በቂ ውይይት ባለመደረጉ/አሳታፊ ባለመሆኑ/ና የአካባቢውን ነዋሪዎች ይሁንታ አለማግኘቱ እንደሆነ ድርጅታችን ያምናል፡፡ በመሆኑም የአካባቢው አርብቶ አደሮች የህይወትና የኑሮ ዋስትናቸው በአደጋ ላይ የወደቀ እንደሆነ፣ ወይም በፕሮጀክቱ መከፈት ህይወታቸውን ወደተሻለ ደረጃ እንደሚቀየርና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ እና ለቀጣይ ህይወታቸው አኗኗራቸውን፣አመራረታቸውን፣ ባህልና ወጋቸውን ያገናዘበ አስተማማኝ ዘላቂ አማራጭ በፕሮጀክቱ የተካተተ ስለመሆኑ ማረጋገጫና ከተካተተም በቂ የግንዛቤ ማስጨበጥና ማሳመን ሥራ ባለመከናወኑ አርብቶ አደሮቹ ስጋት ላይ መወደቃቸውን ሲገልጹ አድማጭ ባለማግኘታቸው ተቃውሞአቸውን በዚህ መንገድ እንዲገልጹ የተገደዱበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህ ችግር ዘላቂና አስተማማኝ መፍትሄ እስካልተበጀለት ተባብሶ እንደማይቀጥል ማመን ያስቸግራል ወይም በተያዘው የአፈናና ክህደት መንገድ ሩቅ ለመጓዝ አይችልም፡፡

## 1.3. የማኅበራዊ አገልግሎቶች ችግሮች፡-

በሽግግሩ ወቅት ቻርተር ‹‹የተረሱና የተጣሉ አካባቢዎች›› ከተባሉት ዞናችን/በወቅቱ ክልል 10/ አንዱ ነው፡፡ በቻርተሩ በዚህ ሥያሜ ከተጠሩት አካባቢዎች ዛሬም ‹‹ተረስቶና ተጥሎ›› የሚገኘው ዞናችን ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ዛሬም በልማትና መልካም አስተዳደር ወደኋላ የቀረ ብቻ ሳይሆን ለባለስልጣናትና ካድሬዎች ተላልፎ የተሰጠ የግል ንብረት ሆኗል ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ህዝቡ መንግስት በሚያካሂደው የልማት እንቅስቃሴ ከመገለሉ በተጨማሪ በአገልግሎቶች ተጠቃሚ በመሆን ፋንታ ተጎጂ እየሆነ ነው፡፡ ለአብነትም፡-

1.3.1. የኤሌክትሪክ ኃይልና መብራት አገልግሎት መቆራረጥ በህዝቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ከሚያደርሰው ጫና በተጨማሪ በተደጋጋሚ በደረሱ የትራንስፎርመሮች ፍንዳታ በመገልገያዎች ላይ ከሚደርሰው ውድመትና በሰው አካል ከሚደርሰው ጉዳት አልፎ ህይወት እየጠፋበት ነው፡፡

1.3.2. በዞኑ የስልክም ሆነ የኢንተርኔት ግንኙነት የለም ከሚባልበት ደረጃ በመድረሱ ፣እንዲሁም በኃይል እጥረቱ ምክንያት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ስለሚቋረጥ ዞናችን ከዓለም ተነጥሎ መኖር ተገዷል ማለት ይቻላል፡፡

1.3.3. ከኤሌክትርክ ኃይል እጥረት አንጻር የተገናኙ የህክምና፣ የትምህርት፣ የአስተዳደር …አገልግሎቶችም በዚያው መጠን እየተደናቀፉ ህዝቡ በአገልግሎት እጥረት ከሚደርስስበት መጉላላትና በመማር ማስተማር ላይ ከሚያስከትለው ጫና በተጨማሪ በእህል ወፍጮ አገልግሎት እጥረት ምክንያት አንድ ደረቅ እንጀራ እስከ 7፡00 ብር እያተሸጠ የኑሮ ውድነቱን ከማይደረስበት ርቀት እየሰቀለው ነው፡፡ በነዚህ ድምር ውጤትም ህዝባችን ሞት ለሚያስከትሉ ችግሮች ጭምር እየተጋለጠ ነው፡፡

## 1.4. በዞኑ የሚገኙ ከተሞች በተለይም የጂንካ ከተማ ልማት ችግሮች፡-

በዞኑ በሚገኙ ከተሞች ልማት ጉዳይ ህዝቡ የሩቅ ተመልካች ከመሆኑም በተጨማሪ በራሱ የሚያደርገው መፍጨርጨርም በማይጠየቁ ካድሬዎች ቤት በማፍረስ ዘመቻ እየተመታ ነው፡፡ ለአብነትም በቀይአፈር ከተማ የተደረገውን እንዲሁም በጂንካ ከተማ በፀጥታና ደህንነት ሥም በአቶ ተስፋዬ ጣሰው (የፍትህ፣

ጸጥታና ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ) የሚመራና ራሳቸው ባደራጁቸው ቡድኖች የሚታገዝ ህገወጥ ድርጊት እየፈረሱ ያሉት የከተማው መስተዳድር እንኳ የማያውቃቸው የቤት ማፍረስ ዘመቻዎች ‹‹ሃይ-ባይ›› ማጣትና ህዝቡን ለስቃይ የዞኑን ሃብት ለውድመት የሚዳርገውን እርምጃ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህንን ህገወጥ ድርጊት ድርጅታችን ሲጠይቅ አግባብ ያለው መልስ ከመስጠት ይልቅ በአደባባይ የሚያሰሙት የውንጀላ ቃላት ህዝቡን ለማስፈራራት ለሚደረገው የአፈና ተግባር ተጨባጭና ግልጽ ማስረጃ ነው፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው በከተማው በመንግስት የተጀመሩ የልማት ስራዎች ለዓመታት እየተጓተቱ ባሉበት እውነት ውስጥ መሆኑ ድርጊቱ ከግል ፍላጎትና ግለሰቦች አይጠየቄነት የተያያዘ መሆኑን ያሳያል፡፡

**<u>2ኛ/ በመታየት ላይ ያለው የምግብ እጥረትና ቀጣይ ስጋት ፤</u>**

በዞናችን ሁሉም የአርብቶአደር ወረዳዎች ህዝብ ከኤሊኒኖ ጋር የተያያዘው የአየር ንብረት መዛባት ለረሃብ ተጋላጭ ሆኗል፡፡ ነዋሪው በረሃብና ተያያዝ በሽታዎች ፣እንስሳት በውሃና መኖ እጥረት ለችጋርና ሞት እየተዳረጉ ነው፡፡ በአንጻሩ እነዚህን ዜጎች ለመታደግ የሚደረግ እንቅስቃሴ አይታይም፡፡ የፌዴራል መንግስት በመጀመሪያ ‹‹ችግሩን ለመደበቅ/መካድ›› ያደረገውን ሙከራ ቀልብሶ ለረጂዎች ተማጽኖና ወቀሳ እያቀረበ መሆኑን የዞናችን ባለስልጣናት የሰሙ አይመስልም፡፡ ጊዜ የማይሰጠው ረሃብ በህዝብና እንስሳት ላይ ‹‹ሞት››ን ይዞ በፍጥነት ለሚያደርገው ጉዞ መግቻ አልተበጀለትም፤ለመከተርም ዝግጅት አልተጀመረም፡፡ ምግብ፣መኖ ውሃና መድሃኒት አልቀረበም ብቻ ሳይሆን ችግሩን አውቆ ለማቅረብ አልታሰበምና ጥፋቱ በሙሉ ኃይሉና በፍጥነት እየተቃረበ ነው፤ ዜጎችና የኑሮ ዋስትናቸው የሆኑት እንስሳት ያለአንዳች መከላከያና ደጀን ከአደጋው ፊት ቆመዋል፡፡ ከነዚህ ተጋላጮች የካራ ብሄረሰብ አገር ሽማግሌዎች ችግሩ ከፍተኛ ጥፋት እያደረሰ መሆኑን በቀጣይም የሚያስከትለው አደጋ አስከፊ ደረጃ ላይ መድረሱን ለማሰማት ረጅም ርቀት ተጉዘው ዞን/ጂንካ ድረስ መጥተው ስንከራተቱ ቆይተው ላሰሙት ጥያቄ መልስ ሳያገኙ ተስፋ ቆርጠው ወደቀያቸው ተመልሰዋል፡፡

የከተማው ነዋሪ ህዝብም ቢሆን ለዚህ አደጋ ተጋላጭነቱ በየዕለቱ እያደገ በሚመጣው የኑሮ ውድነት አየታየ ነው፡፡ በዞኑ የምግብ ምርት/አቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለው ልዩነት ከመቼውም ጊዜ በላይ እየሰፋ መጥቶ ዛሬ ላይ ከኮንሶ የሚመጣው አቅርቦት ለአንድ ቀን/ገበያ ቢቋረጥ የሚደርሰውን ችግር ለመገመት ከሚያዳግትበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ይህ በሆነበት በዞኑ ይህን አሳሳቢ ሁኔታ ከግምት አስገብቶ የመከላከያ እርምጃ ለመውሰድ የሚደረግ እንቅስቃሴ አይታይም፣ ከህዝቡ ጋር ውይይት አልተጀመረም፡፡ ችግሩ አፍጦና አግጦ መልዐከ ሞትን አስከትሎ በፍጥነት እየመጣ ነው፡፡

እነዚህ ችግሮች በሙሉ አሳታፊ ፈጣን ምላሽ ይፈልጋሉ፡፡ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር፣ አሳታፊና በጋራ ለመመከት የሚያስችል በጋራ ማቀድና መፍትሄ ላይ መግባባት፣ በአጠቃላይም የመልካም አስተዳደር ስርዓት መስፈን አለበት፡፡ ይህ ባልሆነበት እንኳን በዜጎች የሚደረገው ቀርቶ በመንግስት የሚመደበውን በጀትም በአግባቡና ለውጤታማ ተግባራት ማዋል የሚቻል አይሆንም፡፡ በተያዘው ችላ ባይነትና ችግሩን የመካድ አካሄድ አፋጣኝ የመከላከል እርምጃ ካልተወሰደ መፍትሄውን በመጎተት እና በመፍትሄ ኃሳቡ ላይ በመጓተት የሚደርሰው ጥፋት የከፋ ይሆናል፣ ህዝባችንን ሰለባ ያደርጋል፣ አላስፈላጊ መስዋዕትነት ያስከፍላል፡፡

ስለዚህ ዛሬም በህዝቡ በተለመደው አሳታፊ የግጭት አፈታት መንገድ በመጠቀም መረጋጋትና ሰላም እንዲሰፍን ፣ ህዝቡን ለይስሙላ ሳይሆን በተጨባጭ በማሳተፍ ለየዞናችን ማኅበረ-ኢኮኖሚ ችግሮች መፍትሄ እንዲበጅለት ስንጠይቅ ፤ ለመፍትሄው በሚደረገው ጥረትም ሆነ ለዞናችን መረጋጋት፣ሰላምና ልማት በሚደረገው እንቅስቃሴ ድርጅታችን ለመወያየትና የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመጨረሻም ዛሬ በዞናችን የምታዩት ችግሮች በአጠቃላይ በአገራችን የሚታዩት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ምስቅልቅሎችና የሰብዐዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ረገጣ ነጸብራቆች መሆናቸውን ድርጅታችን ያምናል፡፡ በመሆኑም ለእነዚህ ዓይነቶቹ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ በብሄራዊ መግባባት ላይ በመድረስና ዕርቅ በማውረድ ህዝባችን በአገራዊ ጉዳዮች ላይ በሚደረስ መግባባት መሰረት በጋራ እንዲቆም ማስቻልና ማሳተፍ በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት የተገባውን ቃል በተግባር እንዲተረጉሙ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡**

**ከሠላምታ ጋር//**

**ዓለማየሁ መኮንን፤**
**ም/ሊቀ መንበርና የዞኑ ጽ/ቤት ኃላፊ፤**

**ግልባጭ፡-**
**ለደቡብ ብ/ብ/ህ/ብ/ክ/መንግስት**
**<u>ሃዋሳ</u>**

**ለሰብዐዊ መብት ጉባኤ/ሰመጉ/**
**ለድርጅታችን ዋና ጽ/ቤት**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

**ለጂንካ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት**
**<u>ጂንካ</u>**

**ፖ.ሣ.ቁ.** 20893
**አአ**
**ስልክ ቁ .** 0113 487666/
0911 408122 /
0916 853625

[**ኢትዮሚድያ** - Ethiomedia.com]
November 18, 2015